# ስፈራ ለአካባቢ መራቆት ምክንያት መሆኑ በጥናት ተረጋገጠ

## መሬት አልባነት የወደፊቱ ከፍተኛ አደጋ ሊሆን ይችላል

በብርሃኑ ፈቃደ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጂኦግራፊና የአካባቢ ጥናቶች ትምህርት ክፍል በታሪኩ የመጀመርያው የሆነውን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት በማድረግ ለምግብ ዋስትና የሚካሄዱ የሰፈራ ፕሮግራሞች አካባቢን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያራቁቱ ሁለት ምሁራን አረጋገጡ:: ከዚህም በላይ በአፈር ለምነት መራቆትና መጎዳት ‹‹እየሞቱ ያሉ መሬቶች›› ከመኖራቸውም በላይ፣ በመሬት ጥበት ሳቢያ መሬት አልባነት የወደፊቱ ከፍተኛ አደጋ እንደሚሆን የሌላኛው ምሁር የጥናት ውጤት ያመላክታል::

አቶ መሳይ ሙሉጌታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እያገለገሉ ያሉና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ሲከታተሉ የቆዩ ናቸው:: ምሁሩ በሰፈራና በምግብ ዋስትና ላይ ያጠነጠነውና በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ ላይ በሚኖሩ 1,800 አባወራዎች ላይ በተካሄደው ጥናታቸው እንደሚያመላክተው፣ የሰፈራ ፕሮግራም ምንም እንኳ ጊዜያዊ የምግብ ዋስትናን በመጠኑ ሊያረጋግጥ ቢችልም ነገር ግን ከፍተኛ የአካባቢ ውድመት አስከትሏል::

በኖኖ ወረዳ ሰፋሪዎች ከመምጣታቸው በፊት የተራቆተና በእርሻ ምክንያት የተመነጠረ መሬት አምስት በመቶ እንደነበር፣ የሰፋሪዎቹን መምጣት ተከትሎ ግን የመራቆቱ መጠን ወደ 25 በመቶ መጨመሩን በጥናታቸው አረጋግጠዋል:: ሰፋሪዎቹ ለእርሻ መሬት ምንጣሮ፣ ለእርሻ ቁሳቁስነት፣ ለቤት ግንባታ፣ ለማገዶነትና ለመሳሰለው ተግባር የአካባቢውን ዛፍ በመመንጠራቸው ምክንያት አካባቢው ለጉዳት መዳረጉ የጥናቱ ውጤት መዳረሻ ነው:: ጥናቱ ይህንን ቢያመላክትም፣ ሰፋሪዎች ከበፊቱ የተሻለ ኑሮ ላይ ስለሚገኙ ዕርዳታም

ወደ ክፍል-1 ገጽ 37 ዞሯል

# ስፈራ ለአካባቢ...

ሆነ ሴፍቲኔት እንደማያስፈልጋቸው አጥኚው አቶ መሳይ ያረጋገጡ ሲሆን፣ ባህላዊ መስኖን በመጠቀም ጥሩ የበቆሎ ምርት ማግኘት እንደቻሉም ይናገራሉ:: ይህም ቢሆን ግን በአካባቢው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት የሰፈራ ፕሮግራም ዘላቂ የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ እንደማይችል ተመልክቷል:: በ1996 እና በ1997 ዓ.ም ሰዎችን ወደ ኖኖ ወረዳ ለምግብ ዋስትና ሲባል ከተራቆቱ አካባቢዎች በማዛወር ማስፈር እንደተቻለ መረጃዎች ያመለክታሉ::

አጥኚው አካባቢው ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመተንተን የተለያዩ ሦስት ጊዜያትን በአመልካችነት ተጠቅመዋል:: የመጀመርያው በ1976 ዓ.ም. ሰፋሪዎቹ ወደ አካባቢው ከመዛወራቸው በፊት የነበረው የአካባቢው ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር የሚያሳይ የጊዜውን የሳተላይት መረጃና ዲጂታል ካርታ ተጠቅመዋል:: እንደገና በ1981 ዓ.ም. ተመሳሳይ መረጃ የተጠቀሙ ሲሆን፣ ሰፋሪዎቹ በአካባቢው ከሰፈሩ በኋላ የታየውን ለውጥና ይዘትም በተመሳሳይ መንገድ በ1999 ዓ.ም. የነበረውን መረጃ ተንተርሰው አጥንተዋል:: ከእንግሊዝ ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ በመጡት ዶክተር ሊዝ ዋትሰንና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ዶክተር ደገፋ ቶሎሳ ከተገመገመ በኋላ በጥሩ ውጤት ዶክትሬታቸው እንደፀደቀ ለማወቅ ተችሏል::

በሌላ በኩል የመሬት ተስማሚነትን ከዝናብ ተኮር ዘላቂ ግብርና ጋር በማያያዝ ጥናት ያደረጉት አቶ አባተ ሽፈራው ናቸው:: የዶክትሬት ጥናታቸው የተገመገመው ከደቡብ አፍሪካው ፍሪ ስቴት ዩኒቨርሲቲ በመጡት ዶክተር ፓል ለሮኸ እንዲሁም በጂኦግራፊና በአካባቢ ጥናቶች ትምህትር ክፍል ኃላፊው ዶክተር ሞሐመድ ሐሰን ነበር:: ጥሩ ውጤት የተመዘገበበት ጥናት ተብሏል::

የአቶ አባተ ጥናት እንደሚያመለክተው በደቡብ ወሎ ዞን፣ ቦረና ወረዳ የለጋማራ ውኃ ተፋሰስ አካባቢ ዝናብን ጠብቆ በሚካሄድ እርሻ ገበሬዎች የሚተዳደሩበት ቢሆንም፣ በከፍተኛ ጎርፍ የሚጠቃ በመሆኑ አስቸኳይ የመሬት ጥበቃ ሥራ ያስፈልገዋል::የመሬቱ ጉዳት ከፍተኛ ስለሆነም ሕዝቡን ማዕከል ያደረገ የመልሶ ማልማት ሥራ አንገብጋቢ ነው ተብሏል::

ለመሬቱ ጉዳት መንስዔ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል የሕዝቡ የመሬት አጠቃቀም፣ ማለትም ተዳፋት መሬት የማረስ ልምዱ፣ የደን መጨፍጨፍ፣ የመሬቱ አቀማመጥ ተዳፋትና ዳገታማ መሆን ከመሬት ይዞታው ጋር ተዳምሮ ይዘቱን እንዳራቆቱት ተረጋግጧል::

እክሰስ ...